# `አዲዮስ እሹሩሩ!`፡ የስንብቱ አንዲት አፍታ

በErmyas A Alula

`አዲዮስ እሹሩሩ` በመጽሐፉ ሶስተኛ ክፍል ጥቁር በተባለው የመጀመሪያ ምዕራፍ ስር የምትገኝ የአንድ ገጽ ከምናምን ንዑስ ምእራፍ ናት። ባለታሪኩ ሚኒሊክ ባዩ ምንነቱ ባልታወቀ በሽታ ከሞተ በኋላ ዳግም ተነስቶ ሕይወቱን እንዲናዘዝ ግማሽ አምላክ በሆነው ስንዝሮ ስለተነገረው ከሞት ይነሳና የኖረውንና የሰራውን ክፉና ደግ፤ ያየውን፣ የሰማውን፣ ያወራውን፣ የዳሰሰውንና ያሸተተውን፤ የተሰማውንና ያደረገውን በቴፕ ሬከርደር ይቀዳል።[ገጽ፡ 337፣ 338]

ጥቁር የሚኒሊክ ባዩ ኑዛዜ ተረክ ነው።

እንደ ታሪኩ አቀራረብ የሚኒሊክ አሟሟትና ትንሳኤ ምሥጢር ከዚህ ትዕይንት ዘግይቶ ቢመጣም፥ የዚህችን ትንጥ ትዕይንት ሥጋ ደግፎ የያዘው አከርካሪ ተረክ እንደሚከተለው ነው።

ከመሞቱ ጥቂት ቀናት አስቀድሞ ምኒልክ ባዩ ከጓደኞቹ[እና በፎቶው ላይ እሹሩሩ ተብላ ከተጠቀሰችው የዓይን ፍቅሩ] ጋር በልጅነት የተነሳውን ጥቁርና ነጭ ፎቶ እያየ በምሽት ጭር ባለ መንገድ ይነዳል። መኪናውን በፍጥነት ይነዳል።

ጭር ባለ የምሽት ጎዳና ላይ መስመጥ በጀመረች ጸሐይ ውጋጋን ፎቶውን አየሁት። ነፋስስልክ ሁለተኛ ደረጃ የተነሳነው አንድ ጥቁርና ነጭ ፎቶ ነበር። ሁልጊዜ መኪናዬ ኪስ ጋቢና የማስቀምጠው። [መስመር 1]
አዳም ሲጽፍ ከባባድ ትዕምርታዊ ድርጊቶችንና ቅርጾችን ይጠቀማል። ይኽን ሲያደርግ አውቆም ይሁን ሳያውቅ ሊሆን ይችላል፥ ዘመናዊያን የሥነልቡና አጥኚዎች እንደሚያትቱት። [በሚካኤል ሺፈራው የተጻፈውን `ምሥጢረኛው ባለቅኔ` ተመልከት]

የአዳም ትዕምርታዊነት ሌላ ደረጃ ላይ ነው። ከሲምቦሊዝሞች ሁሉ ቀድሞ ግን ከላይ ያለውን መስመር በጥሞና ላስተዋለ ሰው ግልጽ የሚሆኑ ሶስት ሁኔታዎች አሉ። እነዚሁም ባለታሪኩ፡

1—በዕድሜው/በዘመኑ/በ`መስከረሙ` ማብቂያ/በጀምበሩ መጥለቂያ ላይ መሆኑ፣ አንኮንሺየስሊም ቢሆን እየተተነበየልን መሆኑ፣
2—ያለፈው `መስከረሜ` የሚለው ልጅነቱን መርሳት/ መተው ያልቻለ፤ ከሱ የተጣበቀ፣ ከሱ ዉጪ ንጽህና እና እውነት የለም ብሎ የሚያምን መሆኑ፣
3—በዚህ የጭንቅ ወቅቱም[ውስጣዊ ነውጥ ነውና ሁከቱ ዓ.ነገሩ `ጭር ባለ ጎዳና` ብሎ በመጀመሩ አይሸወዱም] ወዳለፈው ማየቱን አለመተዉ ናቸው።

ፎቶው ላይ `እሹሩሩ` [በትክክሉ ስሟ ፊያሜታ] የሚኒሊክን እጅ ይዛለች። ያሁኗ ሚስቱ ዙፋን/ሳፍሮን ይኽንን ለመጀመሪያ ጊዜ አይታ ስትጠይቀው ዋሽቷታል። ዋሽቶ ሸውዷታል። ነገር ግን እዛው አንቀጹ ሳያልቅ በፊያሜታ መታለሉንና ንጹህ ይመስለው የነበረው ፍቅር በዝምድና [የጎሳ መመሳሰል] ከባድ ሚዛን የተዘረረ መሆኑን ያምናል። እየተቆጨም ቢሆን ይናዘዛል።

ሚኒሊክ ከሁለቱም አይደለም። አምናውም ዘንዱሮውም ጋር ያልተሰናሰለ ሰው ነው። የአዳም ትዕምርታዊነት ተአምር የሚገለጸው እንዲህ ነው። ምኒልክ ከስሙ ጀምሮ ግራ የሚያጋባ ሚና የተሰጠው ገጸባህርይ ሳይሆን አይቀርም።

በታሪክ ገንነው የወጡት ሁለቱም ምኒልኮች አገር ገንቢዎች ናቸው። ቀዳማዊው ምኒልክ ታላቁን የሶሎሞናዊ ሥርወመንግሥት የመሰረተ ሲኾን፤ ዳግማዊው ምኒልክ ደግሞ በአስራዘጠነኛው ምዕተዓመት መገባደጃ በርካታ የግዛት ማስፋፋቶችንና ወረራዎችን በማካሄድ ዘመናዊት ኢትዮጵያን የመሰረቱ ናቸው።

በመጽሐፉ ድሕረቃል እንደተገለጸው ከሆነ የድርሰቱ አንድ ተናጠፍ የአገር ምስረታ ፌማዎች [myths] ናቸው። አሁን ባገሪቱ ያለውን የፌማ አልባነት [mythless] መነሁለል ካየነው፥ በሚኒሊክ ከሁለቱ የመስመራዊ ጊዜ ክንፎች መላቀቅ ሊገለጽ የተፈለገው በሥነጽሁፍ ብቻ የቀረውን የሶሎሞን—ሳባ—ምኒልክ ፌማ አየር ላይ መቅረት ይመስላል።

ትዕይንቱ ይቀጥላል።

—

ጭር ባለ የምሽት ጎዳና ላይ መስመጥ በጀመረች ጸሐይ ወጋገን ፎቶውን ደጋግሜ አየሁት። ወደ አቃቂ በሰቃ መኪናዬን እንደእብድ እየነዳሁ . . . .

አምስት ኪሎሜትሮች ያህል በጂን ቶኒክ ግለት እየተፈጀሁ፣

[አፍሮሽ]. . . . . .ለመሳቅ ሽርመም ያለ ከንፈረከባድ አፍዋ፣ ያቺ እሹሩሩ. . . . [የወገብዋ አያያዝ]፣ ገጽዋ፣ አ ገጽሽ እንደተራራ ገጽ ነው፣ በጋ እያበበ ክረምት የሚጠወልግ፣ ለምለም ሳርማ መልክሽ ስር የደበቅሽው ድንጋያማ ህልም ነበር፣ ያልገባኝ።

—

እነዚህ ጥቂት መስመሮች ዉስጥ የተገለጸው መዓት ነው፤ ብዙ ብዙ ነገር ነው። ሚኒሊክ ፎቶው ያው ብዙ ጊዜ ያየው የለመደው ቢሆንም ደጋግሞ እያየው ነው። ደጋግሞ እያየው በፍጥነት `እንደእብድ` ይነዳል። ፎቶው እድሜ ልኩን የሚከተለው፣ የተከተለው ግዙፍ የእጣፈንታ ናዳ ይመስላል። በመጨረሻ እንደሚያዩት፥ ፊት ለፊት እንደሚጋፈጡት የእድሜ ዘመን ጠላት። ይኸ እየሆነ ደግሞ በፍጥነት እያሽከረከረ ነው። `እንደእብድ` የሚነዳው በደመነፍስ [ወይም በሚጠጣው ጂን ሞቅታ] ነው። ደመነፍሱ ሽሽቱን ነው። ሽሽቱንና ራሱን መጥላቱን ነው። በፍጥነት መንዳቱ፤ ከጊዜ፣ ከአሁንና ከአምና ማምለጥ መፈለጉ ነው። ፎቶውን ደጋግሞ አይቶት የሆነ ነገር የገባው ይመስላል። ያ የገባው ነገር ደሞ እንዲህ `እንደእብድ` የሚያስነዳው ደመነፍሱ መሸሽ፣ `መሰናበት` መፈለጉ ነው። ፎቶውን እያየው [ሳያውቅ] ይሰናበታል። እያየ ፎቶዋን እሹሩሩን ይሰናበታል። ለፊያሜታ ለራሷ ጀምሮ፣ ደግሞ እንደገና ፎቶውን መግለጽ ይጀምራል። ፎቶውን መግለጽ ጀምሮ፣ ደግሞ እሹሩሩን ይናገራታል። ይናዘዛል፣ ይሰናበታታል።

—

[አፍሮሽ]. . . . . .ለመሳቅ ሽርመም ያለ ከንፈረከባድ አፍዋ፣ ያቺ እሹሩሩ. . . . [የወገብዋ አያያዝ]፣ ገጽዋ፣ አ ገጽሽ እንደተራራ ገጽ ነው፣ በጋ እያበበ ክረምት የሚጠወልግ፣ ለምለም ሳርማ መልክሽ ስር የደበቅሽው ድንጋያማ ህልም ነበር፣ ያልገባኝ።

—

በሚቀጥሉት መስመሮች መኪናውን እያሽመጠጠ ፎቶውን ለነፋስ ሰጥቶ እንደጣለው እናነባለን።

—

ነፋሱ እንደመቀስ ነበር። ቀዳዳ ጨርቅ የመሰለ ሳቁም በመሸ`ወድ መርፌ ተጠቅሞ. . . . . . . ከተቃጠለ አንጀቴ ተሰፍቶ የወጣ። እዚህች ሸዋ ላይ እየተቆራረጠ ወደቀ። አይጣፍበት መሳሳቱ፤ አይለበስ አለመያያዙ።

—

ፎቶው ላይ ያለው `ሳቁ` የልጅነቱ ጊዜያት የየዋህነቱ ደስታ ነው። ሳቁ የዚህ የፊያሜታና የመሰሎቿ በግ ሆኖ ሲጎተት የነበረው ሚኒሊክ ባላዋቂነት የፈገገው ፈገግታ ነው። የሌሎች [ሱዶሎጂያ ፋንታስቲካ] መቀለጃ እያለ ያምነው የነበረ ፌማ ነው። ሳቁ ያለፉት፣ የከሸፉት፣ ኋላቀር የተባሉትና የተረሱት ያገራችን ፌማዎች ናቸው። አለኝ ብሎ ሲመካበት የነበረው `እውነት፣ ደስታና የሞራል ልዕልና` ቀዳዳ ጨርቅ የመሰለ እንደሆነ የገባው አሁን ነው። እሱንም መቀስ በመሰለ ነፋስ ያስወስዳል።

እንዳይጣፍበት፣ እንዳይሻሻል፣ እንዳይዘምን በቂ ውፍረት የሌለው፤ ያሞቀኛል ብለው እንዳይለብሱት፣ እንዳይከለሉበት፣ እንዳይሸሹበት ደሞ የተበጣጠሰ መሆኑ።

መሰረቱን ያጣ፣ ርቃን የሆነ፣ የተቆራረጠ፣ የሳሳ፣ ክብደት የማይችል፣ የማያቻችል፣ የማይበቃ የኢትዮጵያ መርሐብሔር ነው ሳቁ። ሳቁ የከሸፉት የሶስት ሺህና የመቶ አመታት ኢትዮጵያዎች ተምሳሌት ነው። የወደቀው ሳቅ የሁለቱ ሚኒሊኮች የሐገር ምሥረታ ተረኮች ትዕምርት ነው። ስንብቱም ይህንን ክሽፈት መራቅ ነው። የወደቀ አይነሳም የሚሉት ይሄኔ ነው?

[የታሪኩ አቀማመጥ ከኋላ ወደፊት ነውና ደግሞ፥ ጥቂት ገፆችን ወደፊት አልፎ የተፃፈው የስንዝሮና የባለታሪኩን ምልልስ ስናነብ (ተሸክመሃል፣ ብዙ ተሸክመሃል። ማራገፍ የሚገባህ ብዙ ነገር አለ።) [ገፆች፡ 337፣ 338]፣ እና በ'አዲዮስ እሹሩሩ' ስንብቱን ስንሰማ፥ "በርግጥም ሚኒሊክ ባዩ መሞት ነበረበት" እንላለን]

—

ትዕምርታዊነት፣ ስንብት፣ ቋንቋ፣ ፌማ፣ አገር፣ ትዕይንት፣ እድሜ፣ አ አዳም ብቻ! አ አዳም!